## ቀጥሎ በተዘረዘሩት የኢድመንተን ፖሊስ ኣገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።

ለድንገተኛ 9-1-1 ይደውሉ።

ድንገተኛ ላልሆነ 780-423-4567 ይደውሉ።

የሞባይል መገናኛ #377

መስማት ለማይችሉ፥ 780-425-1231

ለበለጠ መረጃ፥ edmontonpolice.ca ይጎብኙ።

በማሕበራዊ ሚድያ ይከታተሉን።

EDMONTON
**POLICE**
SERVICE

**edmontonpolice.ca/KnowYourRights**

## ኢፒኤስ ፖሊስ ሲያስቆሞት ወይም ሲያነጋግርዎት የእርስዎ ግዴታዎች:

- የፖሊስ ጥያቄዎች መመለስ ግዴታ ኣይደለም።
- ለእስር የሚዳርግ ወይም ትኬት የሚያሰጥ የከተማ ደንቦች ይሁን የኣውራጃ/ክልል ህጎች ከጣሱ የግል መረጃ እንዲሰጡ ይጠበቃል።
- በእስር ላይ ካልሆኑ ወይም ለጸጥታ ማደፍረስ ኣደጋ ካልሆኑ ፖሊስ ንብረትዎ ለመፈተሽ ቢጠይቅ ኣይሆንም ማለት ይችላሉ።
- ካልታሰሩ መሄድ ይችላሉ።
- ከታሰሩ ፖሊስ በሚሰጠው የግል መረጃና ደህንነትዎ በጠበቀ ሁኔታ ወድያውኑ ጠበቃ ማነጋገር ይችላሉ።
- የፖሊሱ ስምና ባጅ ቁጥር የማወቅ መብት ኣለ።
- ፖሊስ ቤት የሚበረብርበት የህግ ትእዛዝ ካልያዘ ወይም ቤት ውስጥ ለመግባት ኣስቸኳይ ነገር ካልተፈጠረ በስተቀር ኣለማስገባት ይችላሉ።
- ፖሊስ ቤት ለመፈተሽ የህግ ትእዛዝ ካለው መጠየቅ ይቻላል።
- መኪና እየነዱ ፖሊስ ካቆምዎት መንጃፈቃድ ፥ የመኪና ምዝገባ ና ኢንሹራንስ መስጠት ኣለቦት።
- በመንገድ ዳር የትንፋሽ ፈተና ከመስጠት በፊት ጠበቃ ማናገር ኣይቻልም።
- በፖሊስ ሲያዙ መብትዎ ከተጣሰ፥ በእኩልነት ካልታዩ ወደ ዋና የኢድመንተን ፖሊስ ኮሚሽን ማመልከት ይቻላል።

ይህ መረጃ በፖሊስና በሰዎች ያለው የስራ እንቅስቃሴ ኣጠቃላይ መረጃ ነው። ሁሉም የሰዎች የተሟላ መብት የያዘ ኣይደለም። ይህ መረጃ የጠበቃ ስራ ተክቶ በግል ሁኔታ ምክር ኣይሰጥም። በጉዳይዎ የግል ጠበቃ ማማከር ኣለብዎት። ከታሰሩ ፖሊሱ የእርስዎ መብት ያነብሎታል። እንዲሁም ነጻ የህግ ምክር ለማግኘት ስልክ ቁጥር ይሰጥዎታል።



## የኢፒኤስ ፖሊስ ሃላፊነትና የህዝብ መብቶች

ወንጀል መከላከል ለህዝብ ደህንነት ጠቃሚ ነው። የኢድመንተን ፖሊስ ኣገልግሎት (ኢፒኤስ) ሃላፊነት ሂወትና ንብረት መጠበቅ ፥ የህዝብ ሰላም ማስፈን፥ ወንጀሎች መከላከልና ለይቶ መፍትሄ ማምጣት ነው። ኢፒኤስ ከማህበረሰቡ ጋር በመተባበር ወንጀል መከላከል ካልቻለ የኛ ዓላማ ማጣራት ነው የሚሆነው።

ሁሉም ደህንነቱ እንዲጠበቅለት መብት ኣለው።የፖሊስ ህጋዊ መሰረት ህዝቡ ዕምነቱ በፖሊስ መጣሉ ነው። የህዝብ ዕምነት ከሌለው ፖሊስ ውጤታማ ስራ ሊሰራ ኣይችልም። ኢፒኤስ የኣከባቢው ችግሮች መረዳት ይፈልጋል። ኢፒኤስ የእያንዳንዱ ኢድመንተን ነዋሪ ሂወት ለማሻሻል ዓላማ በመያዝ ከማህበረሰቡ ጋር በቅርበት በመስራት ወንጀሎች ከመድረሳቸው በፊት መከላከል ነው።

ኢፒኤስ ወንጀል ለመከላከልም ሆነ መፍትሄ ለማፈላለግ ሰዎች ከፖሊስ ጋር የሚያደርጉት መረጃ መለዋወጥ ኣስፈላጊ ነው። ሰዎች ከፖሊስ ጋር ከሚኖራቸው ቆይታ በሚመቻቸው ግዜ ለማድረግ ትቶው የመሄድ ሙሉ ነጻነት ኣላቸው። ይህ ማለት ግን ፖሊስ ሰዎችን ጥያቄ ከመጠየቅ ይታቀባል ማለት ኣይደለም። ነገርግን ለእስር የሚዳርግ ጥፋት ከሌለው በስተቀር ማንም ሰው ሁልግዜ ትቶ የመሄድ መብት ኣለው።

የኢፒኤስ ፖሊሶች ሰለሚያገለግሉት ማህበረሰብ ለማወቅ ከህብረተሰቡ ኣባላት ጋር መቀራረብ ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ ወደ ሰዎች ቀርቦው ንግግር መጀመርን ያጠቃልላል። የኢፒኤስ ፖሊስ ፍትሃዊና ለሁለም በእኩልነት ለማገልገል የሰለጠነ ነው። ለምሳሌ ፖሊስ ሰዎችን መንገድ ላይ ኣቁሞ የሚጠይቀው የጸጥታ ደህንነት የማደፍረስ ኣዝማምያ የሚፈጠርበት ሁኔታ ካለ ወይም ተጨማሪ ወንጀል ለመከላከል ብቻ ነው።

ስለሆነም ከፖሊስ ጋር የሚኖሮት ቆይታ የራስዎ መብት ፥ የፖሊሶች ሚናና የስራ ሃላፊነት ማወቅ ኣስፈላጊ ነው። ቀጥሎ የተዘረዘሩት ኣጠቃላይ መረጃ ስለ ኣንድ ፖሊስ ምን ማድረግ እንዳለበት፥ እርስዎ ማድረግ የሌለቦትና በዚህ ሁነታ ሲገኙ ምን ማድረግ እንዳለቦት የሚያሳይ ነው።

## የኢፒኤስ ፖሊስ ሲያስቆሞት ወይም ስያነጋግርዎት ፖሊሱ ማድረግ ያለበት ግዴታዎች:

- ራሱ ማስተዋወቅ ኣለበት።
- ለምን ሊያስቆሞት ወይም ልያናግርዎት እንደፈለገ ማብራራት ኣለበት።
- እርስዎን ለማሰር ከሆነ ምክንያቱ መናገር ኣለበት።
- ከታሰሩ የግል ማንነት በጠበቀ መንገድ ጠበቃ የመያዝ ምክር መስጠት ኣለበት ።
- ካልታሰሩ መሄድ እንደሚችሉ መናገር ኣለበት ።
- የቤት ብርበራ ወይም ክትትል የሚደረግ ከሆነ የጽሁፍ ትእዛዝ መስጠት ኣለበት።
- በምርመራ ግዜ በምክንያትና በኣክብሮት ማድረግ ኣለበት።
- ያለምክንያት ከመጠን በላይ ሃይል መጠቀም ይሁን በንብረት ኣደጋ ማድረስ የለበትም።
- ለምርመራ የተያዘ ንብረት ካለና እርስዎ ከወንጀል ነጻ ከሆኑ ንብረቱ በ 3 ወር ውስጥ መመለስ ኣለበት። ምርመራው ከ3 ወር በላይ የሚፈጅ ከሆነ ከ3 ወር በላይ ለማቆየት ፖሊሱ የህግ ወረቀት ማቅረብ ኣለበት።